# የቀለም አብዮት (Color Revolution)

1. **የቀለም አብዮት ማለት ምን ማለት ነው?**

የቀለም አብዮት እንቅስቃሴ ሲጀመር ለተወሰነ ጊዜ ሰላማዊ በሆነ የትግል ስልት (none violence) መንግስትን ወይም የፖለቲካ ሰርዓትን መለወጥ የሚል ትርጓሜ ይዞ የቆየ ቢሆንም በጊዜ ሂደት ትርጉሙ እየሰፋ በቀለም አብዮት ስም የሚካሄዱ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በተቀናጀ አመራር ወደ ብጥብጥ (violence) እንዲያመሩ በማድረግ አንድን መንግስት ወይም የፖለቲካ ስርዓትን ለማስወገድ በህቡዕ እና በግልፅ የሚከናወን ሀይልን ጭምር የሚያካትት የትግል ስልት እየሆነ መጥቷል፡፡

2. **የቀለም አብዮት ተዋናዮች እነማን ናቸው የመቀስቀሻ አጀንዳቸውስ ምንድነው?**

የቀለም አብዮት ዋና ዋና ተዋናዮች የውጪ ኒዮሊበራል ሀይሎች፣ በሃገር ውስጥ "በተቃዋሚነት" የተደራጁ ፀረ-ስርዓት ሀይሎች እና በተለያየ ቅሬታ ምክንያት ከጎናቸው እንዲሰለፉ ያደረጉዋቸው የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያካትት ነው፡፡

የቀለም አብዮቱን የሚመሩት የውጪ ሀይሎች ኢላማ ያደረጉት መንግስት እንዲወገድና ስርዓቱ እንዲፈርስ የሚፈልጉበት ዋናው ምክንያት ከስርዓቱ ጋር መሰረታዊ የሆነ የርእዮተአለም ልዩነት አለን በሚል ወይም ደግሞ ኢላማ ያደረጉት መንግስት እና ስርዓት ከእነሱ ይልቅ በአለም አቀፍ የሀይል አሰላለፍ ስርዓቱ ውስጥ በባለንጣነት ወይም ተፎካካሪነት ከፈረጁዋቸው ሌሎች ሀያላን ሃገራት ጋር የጠበቀ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ትስስር አላቸው ብለው በማመናቸው ምክንያት የሚፈጠር ጠላትነት ነው፡፡

በሃገር ውስጥ "በስርዓት ተቃዋሚነት" የተደራጁ የቀለም አብዮት መሳርያ የሆኑ የፖለቲካ ሀይሎች በሃገሪቱ ውስጥ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ የፖለቲካ ስልጣንን ለመያዝ የምንችልበት እድል የለም ብለው በመደምደማቸው ምክንያት ከነዚህ የውጪ ሀይሎች ጋር የተወሰነ የርእዮተአለም ቁርኝት በመፍጠር ህጋዊ ባልሆነ የአመፅ መንገድ በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ ግንባር ፈጥረው የሚንቀሳቀሱ ወገኖች ናቸው፡፡

በተለያየ ቅሬታ ምክንያት ለእነዚህ ሀይሎች ድጋፍ የሚሰጡ የህብረተሰብ ክፍሎች የስራ አጥነት፣ የመልካም አስተዳደርና በአጠቃላይም የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው እና ከሃገሪቱና ከስርዓቱ "የሚገባንን ጥቅም አላገኘንም"፣ "እድልዎ ተፈፅሞብናል" ወይም "የተለየ በደል ደርሶብናል" የሚል ስሜት ያደረባቸው ወይም በተሳሳተ መንገድ ይህንን እንዲያምኑ የአእምሮ እጥበት ስራ የተሰራባቸው (brainwash የተደረጉ) በአብዛኛው ስራ አጥ የሆኑ ወጣት የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያካትቱ ናቸው፡፡

የቀለም አብዮቱ ዓላማ እንዲሳካ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ተዋናዮች በጋራ የማስተሳሰር ጉልበት ያለው የመቀስቀሻ አጀንዳ (guiding idea that binds and motivates all the actors) መኖር የግድ የሚል በመሆኑ በተጨባጭ ፈልጎ ለማግኘት የሚያስቸግር "የጋራ ጠላት (common enemy፣ የጋራ መፈክር (common slogan) አሉባልታና የፈጠራ ወሬ (fake news) በመፍጠር የቀለም አብዮቱ ምክንያታዊነትነትን ለማሳመን ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የውጪና የሃገር ውስጥ ሀይሎች በጋራ የሚያስተሳስር መቀስቀሻ አጀንዳዎችን ከፈጠሩ በኋላ በማህበራዊ ሚዲያና ተመሳሳይ የሆኑ ዘመኑ ያፈራቸው የግንኙነት ዘዴዎችን በመጠቀም በየቻት ሩምና ፌስቡክ በተኮለኮሉ "ሚሊሽያዎቻቸው" አማካይነት መንግስትን ለመለወጥና ስርዓቱን ለመናድ የተቀናጀ እንቅስቃሴ ያካሄዳሉ፡፡

## 3. <u>የቀለም አብዮት የአፈፃፀም ስልቶች ምንድናቸው?</u>

በአሁኑ ወቅት ሰላማዊ ከሚመስል የተቃውሞ እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ ወደ ብጥብጥ እያደገ እንዲሄድ እየተደረገ ያለው "የቀለም አብዮት" የተሰኘው ይህ ዘመናዊ የትግል ስልት በተወሰነ አከባቢ ከሚካሄድ ብጥብጥ (violence)፣ ሰፊ አከባቢ ወደሚሸፍን ብጥብጥ፣ በከተሞች አከባቢ ከሚካሄድ የተቃውሞ እንቅስቃሴ፣ በከተሞችና በገጠር ወደሚካሄድ የአመፅ እንቅስቃሴ፣ ማህበራዊ ይዘት ካለው የብጥብጥ እንቅስቃሴ በአብዛኛው ሀይል በትንሹ ደግሞ ማህበራዊ ይዘት ወዳለው ቀውስ፣ በተመረጠ አከባቢ ከሚካሄድ የብጥብጥ እንቅስቃሴ በሁሉም አከባቢዎች ላይ ወዳነጣጠረ ብጥብጥ፣ በማህበራዊ መረብ አማካይነት ከሚፈጠር ትስስር ወደ አካላዊ ትስስር እያደገ እንዲሄድ የሚደረግና በህዝቦች መካከል የነበረውን ማህበራዊ ቁርኝት እንዲበጠስ ከማድረግ አልፎ አብረው በኖሩ ህዝቦች መካከል ያለውን ሁሉም አይነት ትስስር (ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ...ወዘተ) እንዲቋረጥ በማድረግ በህዝቦች መካከል አጠቃላይ ግጭትና ደም መፋሰስ ተፈጥሮ መጨረሻ ላይም ስርዓቱን ከመናድ አልፎ ሃገር እስከማፍረስ የሚዘልቅ አደገኛ የሆነ የትግል ስልት ነው።

የቀለም አብዮተኞች የማይፈልጉትን መንግስትና ስርዓት ለማዳከም፣ ለማንበርከክና ብሎም ስርዓቱንና ሃገሩን ለማፍረስ የሚጠቀሙባቸውና በቅደም ተከተል ተግባራዊ የሚያደርጉዋቸው የተለያዩ የአፈፃፀም ስልቶችም አሉ። ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

### 3.1. <u>መንግስትና ገዥው ፓርቲ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው መስራት</u>

መንግስት እና ገዥው ፓርቲ በህብረተሰቡ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ከሚያከናውኑዋቸው ተግባራት መካከል፡-

- መንግስት በሚከተላቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ ፖሊሲዎችና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ የሆነ ቅሬታ እንዲፈጠር በመስበክ በህብረተሰቡ ውስጥ "የለውጥ ፈላጊነት መንፈስ" እንዲፈጠር ማድረግ፣
- ይህንን የቅሬታ መንፈስ በተቀናጀ የፖለቲካ፣ የፕሮፖጋንዳና የስነልቦና ዘመቻ እንዲስፋፋ በማድረግ መንግስት ተአማኒነት እንዲያጣ ማድረግ፣
- የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተሳሳተ መንገድ በማነሳሳት በመንግስት ተቋማት ላይ እምነት እንዲያጣ ማድረግና ለስርዓት ለውጥ ምቹ የሆነ መንፈስ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ፣
- በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሰራተኛና ተማሪዎች ማህበራትና ሌሎች አደረጃጀቶች ላይ ያነጣጠረ የስርገትና የፕሮፖጋንዳ ሥራ በመስራት መላውን ህብረተሰብ ለማዳረስ ጥረት ማድረግ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 3.2.<u>የህግ የበላይነት እንዲሸረሸር በማድረግ የመንግስትን ህግና ስርዓት የማስከበር አቅም ማዳከም</u>

ህብረተሰቡ በመንግስት ሰላምና ፀጥታ የማስከበር አቅም ላይ እምነት እንዲያጣ ለማድረግ ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች መካከል፡-

- ህዝቡ ለህግና ለስርዓት እንዳይገዛ፣ ህግን መጣስና ህገወጥነትን ማበረታታት፣ ለፖሊስና ለህግ አስከባሪ አካላት እንዳይታዘዝ፣ የፀጥታ አካላትን እንዲዳፈርና ግጭት እንዲፈጥር መገፋፋት፣
- ስፋት ያለው ማነሳሳት፣ አለመረጋጋት፣ ቅሬታ መፍጠር፣ ሥራ ማቀዛቀዝ፣ ከስራ ገበታ መጥፋት፣ የስራ ማቆም አድማ ማድረግ፣
- በፀጥታ ተቋማት (መከላከያ፣ ደህንነት) እና በህግ አስከባሪ አካላት (ፖሊስ፣ አቃቤ ህግ የፍትህ አካላት) ላይ የተቀናጀ የፕሮፖጋንዳና የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ በህብረተሰቡ ውስጥ ጥርጣሬ መፍጠርና ተቀባይነት እንዳይኖራቸው መስራት፣

## 3.3.<u>በመንግስት ላይ ተፅእኖ የሚፈጥሩ ህቡዕና ግልፅ ጥቃቶችን በማስፋፋት ስርዓቱንና ሃገሪቱን ማፍረስ</u>

በዚህ ዙርያ ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፤-

- በተለያዩ የልማት አውታሮችና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የሳቦታጅ፣ የአሻጥር ስራዎችን በመስራት እና የተለያዩ ጥቃቶችን በመፈፀም ኢኮኖሚውን ማዳከም፣
- ዋና ዋና አውራ መንገዶችን በመዝጋት፣ የህዝቡን ነፃ እንቅስቃሴ መገደብ፣ የአቅርቦት እጥረት እንዲፈጠር ማድረግ እንዲሁም የመንግስት ደጋፊ በሚባሉ ግለሰቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች

ህይወትና ንብረት ላይ የተጠናና የታቀደ ጥቃት በመፈፀም ህዝቡ ለመንግስት የሚሰጠውን ድጋፍ አቁሞ በፍራቻና በስጋት የእነሱ ተባባሪ እንዲሆን ማስገደድ፣

- በፖሊስ ሀይል፣ መከላከያና ሌሎች የፀጥታ ተቋማት ውስጥ ስርገት በመፈፀም ህግንና ስርዓት የማስከበር መንፈሳቸውንና የማድረግ አቅማቸውን መሸርሸር፣
- ገዥው ፓርቲና አመራሩን በመከፋፈል መንግስት ሀገር የመምራት አቅሙን ማዳከም፣
- የብጥብጥ አድማሱን በማስፋት አጠቃላይ ስርዓት አልበኝነት እንዲነግስ ማድረግ፣
- በህቡእ በተደራጁ ሀይሎች አማካይነት መለስተኛ የደፈጣ ጥቃቶችንና ቀስ በቀስም ሰፋፊ የደፈጣ ጥቃቶችን በመፈፀም የፀጥታ ሀይሎችን ትኩረትና አቅም መበተን፣
- በመንግስትና ገዥው ፓርቲ ውስጥ መከፋፈል እንዲፈጠር በማድረግ ስርዓቱ ከውስጥ እንዲናጋና እንዲፈረስ ማድረግ

## 3.4. <u>ማህበራዊ ሚድያን በስፋት መጠቀም</u>

በማህበራዊ ሚድያዎች (social media) አማካይነት ቃላትን በመሳርያነት መጠቀም (using words as a weapon) ዋነኛው ስልታቸው ሲሆን በዚህ ዙርያ ከሚያከናውኑዋቸው ተግባራት መካከል

- ሐሰተኛ ወይም የተጭበረበረ ወሬ ማሰራጨት (fake news)
- የጥላቻ ሰበካ/ንግግር ማካሄድ (hate speech)
- የተቀነባበረ የፈጠራ ፎቶግራፍና ምስል ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ በሌላ አገር የተፈፀመን ሁኔታ የሚያሳይ የፎቶግራፍ ወይም የቪድዮ ምስል ኢላማ በተደረገው ሃገር መንግስት እንደተፈፀመ አድርጎ አቀነባብሮ ማቅረብ (well organized social media usage and circulating reconstructed videos) የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

መጋቢት 11 ቀን 2010

**ተፈሪ ቢያድግልኝ**
**ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ**

**<u>ማሳሰቢያ</u>**

በሌሎች አገሮች የተፈፀሙ ድርጊቶችን በማቀነባበር በአገራችን የተፈፀሙ ለማስመሰል ተቀነባብረው ከተዘጋጁና በተለያዩ ማህበራዊ ሚድያዎች ከተሰራጩ በርካታ የፈጠራ ፎቶግራፎች መካከል የተወሰኑትን ከስር ይመልከቱ፤-

1. የደቡብ አፍሪካ ፖሊስ ጆሃንስበርግ ከተማ እ.ኤ.አ ጥቅምት 10 ቀን 2007 አመፅ ባስነሱ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የፕላስቲክ ጥይት ሲተኩስ የተነሳው ፎቶግራፍ በማቀናበር በኢትዮጵያ ውስጥ መጋቢት 15 ቀን 2018 እንደተፈፀመ ለማስመሰል የተሰራ የፎቶ ቅንብር




2. በኤርትራ ስታድዮም ውስጥ በኢትዮጵያ ተፈፀሙብን የሚሉትን በደል ለማሳየት የቀረበ ድራማ አሁን በወያኔ በመፈፀም ላይ ያለ "ግፍ" እንደሆነ አድርገው የሻዕቢያ የሶሻል ሚድያ ሰራዊት አባላት የሰሩት የፎቶ ቅንብር ከስር ይመልከቱ





3. በቅርቡ ነውጦኞቹ በኢትዮጵያ የነዳጅ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ላይ ያስተላለፉትን ማስጠንቀቂያ ተላልፈው በተገኙት የነዳጅ ቦቴዎች ላይ የተወሰደ እርምጃ በማለት የለጠፉት ፎቶግራፍ ፓኪስታን ከደረሰ የአሸባሪዎች ጥቃት የተወሰደ ነው፡፡

